# JBB-R ፖሊሲ- የጥቃት አቤቱታ ምርመራ አሰራሮች

I. ሪፖርት አደራረግ

ማናቸውም ተማሪ በተማሪ፣ በአስተማሪ፣ በአስተዳዳሪ ወይም በማናቸውም ሌላ በስኩል ዲስትሪክቱ አመራር ስር የሚከናወኑ የስፖርት ዝግጅቶች እና ሌሎች ከስርዓተ ትምህርት ጎን ለጎን የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች (extracurricular activities) ጨምሮ በሚደረግ እንቅስቃሴ ላይ በሚሳተፍ፣ ወይም እንዲታዘብ የተመደበ የስኩል ዲስትሪክቱ ሠራተኛ በዘሩ/ዋ፣ በጎሳው/ዋ፣ በጾታው/ዋ፣ በጋብቻ ሁኔታው/ዋ፣ በምንጭ ብሔሩ/ሯ በሃገሩ/ሯ፣ የአካል ጉዳቱ/ቷ፣ ሃይማኖቱ/ቷ፣ ዕድሜው/ዋ፣ የወሲብ ዝንባሌው/ዋ ወይም የጾታ ምንነቱ/ቷ ላይ በመመርኮዝ የወሲብ ጥቃት ወይም በደል ተፈጽሞብኛል ብሎ/ላ ካመነ/ች ፣ ይህን መሰሉ ጥቃት/በደል በአስቸኳይ በዚህ ፖሊሲ መሰረት ለተሾመ ለሚመለከተው የስኩል ዲስትሪክት ባለስልጣን ሪፖርት እንዲያደርግ/እንድታደርግ ይበረታታል/ትበረታታለች።

ማናቸውም አስተማሪ፣ አስተዳዳሪ ወይም የት/ቤት ባለስልጣን አንድ ተማሪ በተማሪ፣ በአስተማሪ፣ በአስተዳዳሪ ወይም በማናቸውም ሌላ በስኩል ዲስትሪክቱ አመራር ስር የሚከናወኑ የስፖርት ዝግጅቶች እና ሌሎች ከስርዓተ ትምህርት ጎን ለጎን የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች (extracurricular activities) ጨምሮ በሚደረግ እንቅስቃሴ ላይ በሚሳተፍ፣ ወይም እንዲታዘብ የተመደበ የስኩል ዲስትሪክቱ ሠራተኛ በዘሩ/ዋ፣ በጎሳው/ዋ፣ በጾታው/ዋ፣ በጋብቻ ሁኔታው/ዋ፣ በምንጭ ብሔሩ/ሯ በሃገሩ/ሯ፣ የአካል ጉዳቱ/ቷ፣ ሃይማኖቱ/ቷ፣ ዕድሜው/ዋ፣ የወሲብ ዝንባሌያው/ዋ ወይም የጾታ ምንነቱ/ቷ ላይ በመመርኮዝ የወሲብ ጥቃት ወይም በደል ተፈጽሞብኛል ብሎ/ላ ሪፖርት ከተደረገለት፣ ይህን መሰሉ ጥቃት/በደል በአስቸኳይ በዚህ ፖሊሲ መሰረት ለተሾመ ለሚመለከተው የስኩል ዲስትሪክት ባለስልጣን ሪፖርት ማድረግ አለበት።

ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች ምክንያት አንድ ተማሪ የወሲብ ጥቃት ሰለባ እንደሆነ/ች ወይም በደል እንደደረሰበት/ባት ዕውቀቱ ያለው ወይም በደል ተፈጽሟል ብሎ የሚያምን ሌላ ማንኛውም ግለሰብ ይህን መሰሉ ጥቃት/በደል በአስቸኳይ በዚህ ፖሊሲ መሰረት ለተሾመ ለሚመለከተው የዲስትሪክት ትምህርት ቤት ባለስልጣን ሪፖርት እንዲያደርግ ይበረታታል።

የስኩል ዲስትሪክቱ ሪፖርት አድራጊው ወይም በግል አቤቱታ አቅራቢው ከእያንዳንዱ ት/ቤት ላይ ወይም ከርዕስ 9 ሹም (Title IX Officer) ማግኘት የሚቻለውን ሪፖርት ማድረጊያ ቅጽ እንዲጠቀሙ ይበረታታሉ፣ ነገር ግን በቃል የሚቀርቡ ሪፖርቶችም እንደ አቤቱታ ይቆጠራሉ። ኦፊሴላዊ የሪፖርት ማድረጊያ ቅጾችን መጠቀም ግዴታ አይደለም። በዚህ ፖሊሲ የተቀመጠ አንዳችም ነገር አንድን ግለሰብ የደረሰ ጥቃትን በቀጥታ ለርዕስ 9 ሹም (Title IX Officer) ወይም ለሱፐር ኢንቴንደንቱ ሪፖርት ከማድረግ ሊያሰናክለው አይችልም።

A. በየእያንዳንዱ የት/ቤት ሕንፃ። የት/ቤቱ ርዕሰ መምህር በት/ቤት ደረጃ የደረሰ ጥቃትን በቃል ወይም በጽሑፍ ሪፖርት የመቀበል ኃላፊነት ያለበት ግለሰብ ነው። ማናቸውም የጥቃት ሪፖርት የተቀበለ የስኩል ዲስትሪክት ሠራተኛ ወዲያውኑ ይህንኑ ለት/ቤቱ ርዕሰ መምህር ማሳወቅ አለበት።

የት/ቤቱ ርዕሰ መምህር ሪፖርት ከደረሰው በኋላ፣ የቀረበው አቤቱታ ላይ የሚደረገውን የማጣራት ምርመራ ሥራ ለሚያስተባብረው ለርዕስ 9 ሹም (Title IX Officer) ያሳውቃል። አቤቱታው ራሱን የት/ቤት ርዕሰ መምህሩን የሚመለከት ከሆነ፣ ሪፖርቱ በቀጥታ ለርዕስ 9 ሹም (Title IX Officer) ወይም ለሱፐር ኢንቴንደንቱ መቅረብ አለበት።

B. በዲስትሪክት ደረጃ። የትምህርት ቤቱ ቦርድ ርዕስ 9 ሹምን (Title IX Officer) ከት/ቤት ርዕሰ መምህራን ወይም ከግለሰቦች በተማሪዎች ላይ የደረሱ የወሲብ ጥቃት ሪፖርቶችን ወይም አቤቱታዎችን እንዲቀበል ሾሞታል። ማናቸውም በማዕከላዊ ቢሮዎች ውስጥ ያለ የጥቃት ሪፖርት የተቀበለ የስኩል ዲስትሪክት ት/ቤት ሠራተኛ ወዲያውኑ ይህንኑ ለርዕስ 9 ሹም (Title IX Officer) ማሳወቅ አለበት። አቤቱታው ራሱን ርዕስ 9 ሹም (Title IX Officer) የሚመለከት ከሆነ ሪፖርቱ በቀጥታ ለሱፐር ኢንቴንደንቱ መቅረብ አለበት።

C. የስኩል ዲስትሪክቱ የዚህን ጸረ ወሲባዊ ጥቃት እና በደል ፖሊሲን የተጨመቀ አጭር ማጠቃለያ ጽሑፍ እንዲሁም የርዕስ 9 ሹም (Title IX Officer) ስምን በእያንዳንዱ ት/ቤት እና በእያንዳንዱ የስኩል ዲስትሪክቱ የሚያስተዳድረው ማዕከላዊ ቢሮ ለሁሉም የፋኩሊቲ አባላት፣ አስተዳዳሪዎች፣ እና ሌሎች ሠራተኞች በጉልህ በሚታይ ቦታ ላይ መለጠፍ አለበት። በተጨማሪ፣ ይህ ፖሊሲ በስኩል ዲስትሪክቱ የድር ጣቢያ (ቄብሳይት) በበይነመረብ (ኢንተርኔት) ላይ መለጠፍ አለበት። የፖሊሲው ቅጅዎችን ከእያንዳንዱ ት/ቤት ርዕሰ መምህር ቢሮ እና ከሠራተኞች አስተዳደር መምሪያ ማግኘት ይቻላል።

D. የስኩል ዲስትሪክቱ የቀረበውን አቤቱታ ምስጢራዊነት፣ አቤቱታ የቀረበበትን ግለሰብ እና የምስክሮችን ክብረ ገበና በተቻለ መጠን ስኩል ዲስትሪክቱ በሕግ ጉዳዩን ለመመርመር፣ ተገቢውን እርምጃ ለመውሰድ፣ እና ኃላፊነቶችን ለመወጣት ወይም ለማስፈጸም ያሉበት ሕጋዊ ግዴታዎችን ሳይጣረስ በምስጢር ይይዛል።

II. ምርመራ እና የመፍትሔ ሃሳብ

የተከለከለ ጥቃት/በደል እንደደረሰ ሪፖርት ሲደረግ ወይም አቤቱታ ሲቀርብ፣ ርዕስ 9 ሹም (Title IX Officer) ወዲያውኑ ምርመራ ማድረግ መጀመር አለበት ወይም እንዲደረግ መፍቀድ አለበት።

ምርመራው ከአቤቱታ አቅራቢው፣ አቤቱታ ከቀረበበት ግለሰብ እና ሌሎች ጉዳዩ እንደተፈጸመ ከሚያውቁ ወይም አቤቱታው እንዲቀርብ ምክንያት ስለሆኑ ሁኔታዎች ዕውቀት ያለቸው ግለሰቦች ጋር የሚደረግ ቃለ መጠይቅን ሊያካትት ይችላል። ምርመራው በተጨማሪ ከቀረበው ክስ ጋር ተዛማጅነት ወይም ተገቢነት ያላቸውን ደጋፊ ሌሎች መረጃዎችን ወይም ሰነዶችን ምርመራ ሊያካትት ይችላል።

የቀረበው ክስ በእርግጥ ይህ ፖሊሲ ስለ መጣሱ ለማረጋገጥና ለመወሰን፣ የስኩል ዲስትሪክቱ የሚከተሉትን ነገሮች ከግምት ያስገባል፥

· የተፈጠሩት ነገሮች ሁኔታ እና አገባባቸው

· የቀረበው የጥቃት ክስ በምን ያክል ድግምግሞሽ፣ ለምን ያህል ጊዜ፣ የጥቃቱ ክብደት እና መጠነ ስፋት እንደተፈጸመ

· በጉዳዩ ውስጥ ያሉ ወገኖች ግንኙነት

· የጥቃት ሰለባው ጾታ፣ ዘር፣ ቀለም፣ የወሲብ ዝንባሌ፣ ብሔራዊ መገኛ ምንጭ/ሃገር፣ የአካል ጉዳት፣ ሃይማኖት እና/ወይም ዕድሜ

አንድ ድርጊት ይህን ፖሊሲ ስለ መጣሱ ውሳኔ ላይ ለመድረስ የቀረቡትን ተጨባጭ ማስረጃዎች፣ እውነታዎች እና ሁኔታዎች በሚገባ መመርመር ይጠይቃል።

ርዕስ 9 ሹም (Title IX Officer) ወይም የእርሱ ወይም የእርሷ ወኪል ምርመራውን እንዳጠናቀቀ/ች የምርመራውን ውጤት ለሱፐር ኢንቴንዳንቱ በጽሑፍ ማቅረብ አለበት/ባት። ክሱ ሱፐር ኢንቴንደንቱን ራሱን የሚመለከት ከሆነ የርዕስ 9 ሹም (Title IX Officer) ሪፖርቱን በቀጥታ ለት/ቤቱ ቦርድ ሊያቀርብ ይችላል። ሪፖርቱ የቀረበው ክስ እውነተነት ያለው ስለመሆኑ እና ይህ ፖሊሲ ስለመጣሱ ግልጽ ውሳኔ የያዘ መሆን አለበት።

III. የስኩል ዲስትሪክት እርምጃ

A. ርዕስ 9 ሹም (Title IX Officer) ወይም የእርሱ ወይም የእርሷ ወኪል ለአቤቱታ አቅራቢው እና ክሱ ለቀረበበት ወገን የምርመራ ውጤቱን እና የስኩል ዲስትሪክቱ ከዚህ የምርመራ ውጤት በመነሳት እየወሰደ ያለውን እርምጃ በተመለከተ ማሳወቅ አለበት/ባት። የስኩል ዲስትሪክቱ በግዛቲቱ እና በፌደራል ሕጎች ስለ ክብረ ገበና ነክ ሪኮርዶች ለሌሎች ማሳወቅ ደንብ መሰረት እና የወንጀል ድርጊቱን የፈጸመው ግለሰብ ያሉት የክብረ ገበና መብቶች በማያሳጣ መልኩ መረጃውን ለሌሎች ይሰጣል።

B. ጥቃት/በደል እንደደረሰ ሪፖርት ሲደረግ፣ የስኩል ዲስትሪክቱ ተገቢነት ሲኖረው በጥቃቱ የደረሰውን ጉዳት ለማስተካከል፣ ለጥቃቱ ሰለባ አስፈላጊውን እገዛ መስጠትን ጨምሮ የደረሰው ጥቃትን ለማስቆም፣ በጥቃት አድራሹ ላይ ተገቢውን እርምጃ ለመውሰድ፣ እና ጉዳዩን ለማስተናገድ አፋጣኝ እርምጃ ይወስዳል። የደረሰውን ጥቃት የፈጸመው ሌላ ተማሪ ከሆነ፣ የሚወሰደው እርምጃ የምክር አገልግሎት፣ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና፣ የወላጅ እና መምህር ውይይት፣ ማስጠንቀቂያ መስጠት፣ ከት/ቤት መታገድ፣ መባረር፣ ወደ ሌላ መዛወር እና የመጥፎ ባሕሪ ማረቂያ እርምጃ መውሰድን ሊያካትት የሚችል ቢሆንም እርምጃው በነዚህ ብቻ የተገደበ ሊሆን አይችልም። የደረሰውን ጥቃት የፈጸመው ግለሰብ የስኩል ዲስትሪክቱ ሠራተኛ ከሆነ የሚወሰደው እርምጃ ማስጠንቀቂያ መስጠት፣ ከሥራ መታገድ ወይም ወዲያውኑ ከሥራ መባረር ሊሆን ቢችልም እርምጃው በነዚህ ብቻ የተገደበ አይደለም። ማናቸውም የስኩል ዲስትሪክት በዚህ ፖሊስ መሰረት

የሚወስደው እርምጃ ተገቢነት ካላቸው የሠራተኛ ማህበር ስምምነቶች፣ የስቴት ሕጎች እና የስኩል ዲስትሪክት ፖሊሲዎች ጋር የተጣጣመ መሆን አለበት። የስኩሉ ዲስትሪክት ጥቃትን ለማስቆም እና ጥቃቱ ደግሞ እንደማይፈጸም ለማረጋገጥ እንደ አስፈላጊነቱ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል።

IV. ከበቀል ነጻ መሆን

በቀና ልቦና የቀረበ አቤቱታ ወይም የጥቃት ሪፖርት የአቤቱታ አቅራቢውን ወይም የሪፖርት አድራጊውን የወደፊት የሥራ ዕድል፣ የሥራ ቦታ ድባብ፣ የሥራ ኃላፊነት/ዕድገት፣ የመማሪያ ድባብ ወይም የትምህርት ውጤት ላይ አንዳችም ተጽዕኖ ሊኖረው አይገባም።

በአንድ የወሲብ ጥቃት ወይም በደልን ሪፖርት ያደረገ ግለሰብ ወይም በማናቸውም ስለዚህ የወሲብ ጥቃት ወይም በደል በተመለከተ የማጣራት እና የምርመራ ሂደት ላይ ቀርቦ የምስክርነት ቃሉን በሰጠ ግለሰብ ላይ የበቀል እርምጃ ሲወስድ በሚገኝ ተማሪ፣ አስተማሪ፣ አስተዳዳሪ ወይም ሌላ የት/ቤቱ ሠራተኛ ላይ የስኩል ዲስትሪክቱ የዲስፕሊን እና ሌሎች ተገቢ እርምጃዎችን ይወስዳል። የበቀል እርምጃዎቹ ማናቸውም ዓይነት ማስፈራሪያ፣ ብቀላ ወይም በደልን ሊያካትት ቢችልም መልኩ በነዚህ ብቻ የተገደበ ግን አይደለም።

V. ከጥቃት ነጻ መሆን

የስኩል ዲስትሪክቱ ሁሉም ወሲባዊ ይዘት ያለው ጥሪ ወይም ባሕሪ እንደ ወሲባዊ ጥቃት ሊፈረጅ እንደማይችል ያምናል። አንድ ድርጊት ያለ ምንም መድሎ ድርጊቱ የግል ጉዳይ፣ ማህበራዊ መስተጋብር የሚፈቅደው ስለ መሆኑ ውሳኔ ላይ ለመድረስ የቀረቡትን ተጨባጭ ማስረጃዎች፣ እውነታዎች እና ሁኔታዎች በሚገባ መመርመር ይጠይቃል። በተመሳሳይ መልኩ፣ ሁሉም በጾታ፣ ዘር፣ ቀለም፣ የወሲብ ዝንባሌ፣ ብሔራዊ መገኛ ምንጭ/ሃገር፣ የአካል ጉዳት ወይም ሃይማኖት የተነሳ ደረሱ የሚባሉ ጥቃት ድርጊቶች እንደ ተከተሰቱ የበደል ዓይነቶች ሊፈረጁ አይችሉም። አሁንም እንደገና፣ በደል ስለመድረሱ ሊወሰን የሚችለው የቀረቡት ተጨባጭ ማስረጃዎች፣ እውነታዎች እና ሁኔታዎች በሚገባ ከተመረመሩ በኋላ ብቻ ነው።

VI. ሌላ አማራጭ የአቤቱታ አቀራረብ መንገድን የመምረጥ መብት

ከላይ የተቀመጡት አሰራሮች አንድ ግለሰብ ለደረሰበት በደል ሌሎች ፍትሕ የማግኛ መንገዶችን የመጠቀም መብቱን አይገድቡም።

VII. ወሲባዊ ጥቃት እንደ ወሲባዊ ወንጀል

በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ የወሲብ ጥቃት በስቴት ሕግ መሰረት እንደ ወሲባዊ ወንጀል ሊቆጠር ይችላል። ይህ ሁኔታ ሲያጋጥም፣ የስኩል ዲስትሪክቱ በተቀመጠው የስቴት ሕግ እና በስኩል ዲስትሪክቱ በሕፃናት ላይ የሚደርስ የወሲብ ጥቃት/ወንጀልን በተመለከተ ባስቀመጠው የአሰራር ደንብ መሰረት ግዴታውን ይወጣል።

VIII. የይግባኝ ማለት ሂደት

አቤቱታ አቅራቢው በምርመራው ውጤት ወይም እንደ መፍትሔ እንዲወሰድ በቀረበው እርምጃ ካልረካ፣ ሱፐር ኢንቴንደንቱ ወይም የእርሱ ወኪል ጉዳዩን እንደገና እንዲመረምረው የመጠየቅ መብት አለው። ይህን መሰል እንደገና ጉዳዩ እንዲታይ የሚቀርቡ ጥያቄዎች ጉዳዩ ለምን እንደገና እንዲታይ እንደተፈለገ በግልጽ ማስቀመጥ እና መርማሪው ውሳኔውን በሰጠ ባሉት አምስት ቀናት ውስጥ ወደ ሱፐር ኢንቴንደንቱ ቢሮ መቅረብ አለባቸው። ሱፐር ኢንቴንደንቱ ወይም ወኪሉ እርሱ ወይም እርሷ አስፈላጊ ነው ብሎ/ላ ካመነበት/ችበት ተጨማሪውን ምርመራ ሊያደርግ/ልታደርግ ይችላል/ትችላለች። ሱፐር ኢንቴንደንቱ ወይም ወኪሉ ግምገማውን እንዳጠናቀቀ፣ ውሳኔውን/ዋን በጽሑፍ ያሳውቃል/ታሳውቃለች።

ሱፐር ኢንቴንደንቱ ወይም ወኪሉ የሚሰጡት ውሳኔ የመጨረሻ ይግባኝ የሌለው ገዢ ውሳኔ ይሆናል።

እንዲጣጣም ተደርጎ የተዘጋጀ፥ ማርች 6፣ 1997
እንደገና የተሻሻለው፥ ፌብሩዋሪ 18፣ 1999
እንደገና የተሻሻለው፥ ጁን 16፣ 2000
እንደገና የተሻሻለው፥ ጁን 20፣ 2002

ሕጋዊ ዋቢዎች፥ Title IX of the Education Amendments of 1972, U.S.C. Section 1681, et seq.
Title VI of the Civil Rights Act of 1964, 42 U.S.C. Section 2000d, et seq.
Title II of the Americans with Disabilities Act of 1990, 42 U.S.C. Section 12101, et seq.
Section 504 of the Rehabilitation Act of 1973